# ክብረ ታቦት

«ታቦት» በግእዝ ቋንቋ ማደሪያ ማዳኛ ማለት ነው። በዚሁ መሠረት በጻድቁ በኖኅ ዘመን የፍጡራን ዘሮች ከጥፋት ውኃ የዳኑባት መርከብ በግእዙ ታቦት ይባላል።

ጻድቁ ኖኅ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ታቦት አዘጋጅቶ ስምንት ራሱ ለዘር ከተመረጡት ፍጥረታት ጋር ወደ ታቦቱ ገብቶ ከጥፋት ውኃ ዳነ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝየተከተለ ኖኅን ለእርሱ ከነበሩ ፍጥረታት ጋር በታቦቱ አማካይነት እግዚአብሔር አዳነው (ዘፍጥ.6-8 ያለውን ይመልከቱ)።

በኋላ በዘመነ ሙሴ ደግሞ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያን መገለጫ እንደ ሆነ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ታቦትን አዘጋጀ (ዘጸአ. 25፤ 9-19)። እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ «ወውስተ ታቦት ትወዲ ትእዛዝ ዘአነ እሁበከ» - «እኔም የምሰጥህ ትእዛዝ (አሠርቱ ቃላትን) በታቦቱ ውስጥ ታስቀምጣለህ» አለው። ከዚምም አያይዞ ከታቦቱ እግዚአብሔር ለሙሴእንደሚገለጽለት ነገረው፣ እንዲህ ብሎ «ወእትኤመር ለከ በህየ ፥ ወእትናገረከ እምላእለ ተድባብ ማእክለ ክልኤቱ ኪሩባን እለ ሀለው ዲበ ታቦት ዘመርጡል» - ኪሩቤል ታቦቱን ጋርደው በዙሪያው ወዳሉበት በዚያ ላይ ሆኜ እገለጽልሃለሁ፤ አነጋግርሃለሁም» አለው (ዘጸአ. 25፥22)። በዚሁ መሠረት ታቦት ማለት እግዚአብሔር የሚያድርበትን የሚገለጥበት ለጽላተ ሕጉ ማደሪያ ማለት ነው።

<u>ጥያቄ</u> - ጽላት ማለት ምን ማለት ነው?

<u>መልስ</u> - ጽላት ማለት እግዚአብሔር አሥሩን ትእዛዛት (አሠርቱ ቃለትን) የጻፈበትና የእግዚአብሔር ሕግ ያለበት ማለት ነው። የጽላቱም አመጣጥ እንዲህ ነው።

«እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ሲና ተራራ ጠራው፤ ሙሴም በሲና ተራራ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በጾምና በጸሎት ኖረ፤ ከዚያም እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን ትእዛዝ በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ (ከዕብነ በረድ የሆኑትን ሁለቱን ጽላቶች ሰጠው» (ዘጸአ.31፤18)።

ስለዚህ ጽላት በኦሪት ዘጸኦት ምእራፍ 20 ቁጥር 1 ጀምሮ ያሉትን አሥሩን ቃላት (አሥሩን ትእዛዛት) የያዘ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ሕግ ነው። በእርግጥ ጽላቶቹ ሁለት እንደሆኑ የእግዜአብሔር ቃል ያስረዳል። ቃሉም እንዲህ ይላል፤ «ሙሴም ከተራራው ተመለሰ፤ ሁለቱንም የምስክር (የቃል ኪዳን) ጽላቶች በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ፤ ጽላቶቸም በዚህና በዚያ በሁለት ወገን ተጽፎባቸው ነበረ፤ ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፤ ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽህፈት ነበረ» ይላል (ዘጸአ. 32፥15-17)።
ነገር ግን ሙሴ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር በዚያው በዘገየ ጊዜ ሕዝበ እስራኤል ካህኑንአሮንን አስገድደው አማልክት (ጣዖታት) ሥራልን ብለው አስጨንቀው ያዙት፤«ይህ ከግብጽ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱትን አማልክት ሥራልን አሉት

።» አሮንም «በሚስቶቻችሁ፤ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች/ጉትቻዎች ሰብራች ሁ አምጡልኝ አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ በጆሮዎቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች/ጉትቻዎች አመጡለት። እርሱም ከእጃቸው ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፤ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ ከዚያም - እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብ ጽ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው ብሎ ነገራቸው። ሕዝቡም አሮን ላቆመው ጣዖት መስዋዕትንና ምስጋናን አቀ ረቡ፣ በዓልም አድርገው ሲበሉ፣ ሲጠጡና ሲዘፍኑእግዚአብሔር አያቸው፤ እጅግም ተቆጣና ሙሴን ጠርቶ - ሁር ወ አፍጥን ወሪደ እምዝየ እስመ አበሱ ሕዝብከ ዘአውጻእከ እምድረ ግብጽ፤ - ከግብጽ ያወጣሃቸው ሕዝብ ኃጢአት ሠርተዋልና ሂድ፤ ከዚህ ፍጠንና ውረድ፤ ካዘዝኳቸው መንገድም ፈጥነው ፈቀቅ ብለዋልና ...አለው፤ ቀጥሎም - ር ኢኩ ዘንተ ሕዝበ፤ ወናሁ ዝንቱ ሕዝብ ግዙፈ ክሳድ ውእቱ፤ ወይእዚኒ ኅድገኒ እጥስዮሙ በመዓትየ ወእሰይመከ ላ እለ ሕዝብ ክቡድ ወዐቢይ - እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት፤ እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፤ አሁንምተቆጥቼ አጠ ፋቸዋለሁና ተወኝ፤ አንተንም ታላቅና በረጋ ሕዝብ ላይ እሾምሃለሁ አለው። ሙሴም ይህንን ሰምቶ እጅግ ደነገጠ፤ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ሰለ ሕዝቡ ለመነ፤ እንዲህም አለ - አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ም ድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለምን ተቃጠለ ...ጌታ ሆይ ከመዐትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም ርኅራኄ አድርግ... በራ ስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችን አብርሃምን፤ ይስሐቅንና ያዕቆብን አስብ» ... ብሎ ጸለየ። ከዚህ በኋላ በሙሴ ጸሎት እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ(ሊያመጣ) ካሰበው መቅሰፍት (መዓት) ተመለሰ፤ ርኅራኄንም አደረገ (ዘጸአ. 3 2፥ 1-4)።

ከዚያም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሙሴ ኢያሱን አስከትሎ በቶሎ ወደ ሕዝቡ ወረደ፣ ሕዝቡም የጥጃን ምስል (ጣ ዖት) አቁመው ሲሰግዱ አገኛቸው፤ መንፈሳዊ ቅናት አቃጠለውና በያዛቸው ሁለትየድንጋይ (የዕብነበረድ) ጽላቶች ጣ ዖቱን ሰበረው፤ ጽላቶቹም ጣዖቱን ሰብረው ስለ ተሰበሩ (ዘጸአ. 32፥15-24) ሙሴ እንደገና ወደ እግዚአብሔር አመለከ ተ። እግዚአብሔርም ለሙሴ እንዲህ አለው «ቀር ለከ ክልኤተ ጽላተ ዘእብን ከመ ቀዳምያት ወእርግ ኃቤየ ውሰተ ደብር፤ ወእጽሕፍ ውስተ ውእቶን ጽላት ዝከተ ነገረ ዘሀሎ ውሰተ ቀዳምያት ጽላት ዘቀጥቀጥኮን» - «ሁለት የድንጋ ይ የእብነ በረድ) ጸላቶች እንደ ፊተኞች አድርገህ አዘጋጅ፤ በሰበረካቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃላቶች እ ጽፍባቸዋለሁ»ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው (ዘጸአ. 34፥ 1-3)።

ሙሴም እንደ ፊተኞቹ አድርጎ ሁለት የድንጋይ (ከዕብነ በረድ) ጽላቶች አዘጋጀ፤ እግዚአብሔርም እነዳዘዘው ዳግመ ኛ ወደ ሲና ተራራ ወጣ፤ ሁለቱንም የድንጋይ (የዕብነ በረድ) ጽላቶች በእጁ ወሰደ (ዘጸአ.34፥4-6)። ሙሴም በሴና ተራራ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር እንደ ተናገረው በሁለቱም ጽላቶች ላይ አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎ ች (አሥርቱ ቃላትን) ጻፈባቸው፤ ሙሴም ሁለቱን ጽላቶች ይዞ ከሲና ተራራ ወረደ (ዘጸአ. 34፥26-30)።

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁለቱን ጽላቶች ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አኖራቸው፤ መሎጊያም (መሸከሚያም) በ ታቦቱ ዘንድ አደረገ፤ የሥርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ አኖረው፤ ከዚያም ታቦቱን ወደማደሪያው (ወደ ድንኳኑ) አገባው፣ የሚሸፍነውም መጋረጃ አድርጎ የምስክሩን ታቦት ሸፈነ (ዘጸአ.40፥20-21)።

ጥያቄ፤ ከዚህ በላይ የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተረድተውታል?
መልስ፣ እኔስ እምብዛም አልተረዳሁትም፤ ስለዚህ እባክዎት እንደገና አብራርተው ያስረዱኝ።
መልስ፤ እንግዲያውስ አስተውል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ታቦት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተዘጋጀ የእግዚአብሔር ሕግ ያለበት የጽላት ማደሪያ ነው። ጽላት ደግሞ አሥሩ የእግዚአብሔር ሕጎች (አሥር ትእዛዛት) የተጻፉበት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ምስክር ነው። ስለዚህ የጽላት ማደሪያ የሆነው ታቦት እግዚአብሔር የተገለጠበትና የሚገለጥበት የእግዚአብሔር ዙፋን ነው። በመሆኑም ታቦቱንና ጽላቱን ማክበር ራሱን እግዚአብሔርን ማክበር ነው። ካህናቱና ሌዋውያኑም ታቦቱን ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲወስዱ ወይም ሲያንጉዙ ሙሴና ከሙሴ ጋር የነበሩ ሁሉ «ጌታ ሆይ (አቤቱ)
ተነሣ ፣ጠላቶችህም ይበተኑ፣ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሽሹ» እያሉ ይዘምሩ ነበር። ይኸውም ታቦቱ የእግዚአብሔር መገለጫና መንበር (ዙፋን) መሆኑን በመገንዘብ ነው (ዘኁል. 10፥35)።

እንደዚሁም ሙሴ የእግዚአብሔር ታቦት ወዳለበት ወደ መገናኛው (ወደ መሰብሰቢያ ድንኳን) በገባ ጊዜበቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ካለው ከሥርየት መክደኛው በላይ ከኪሩቤልም (በኪሩቤል አምሳል ከተቀረጹት መላእክት) መካከል የእግዚአብሔርን ድምጽ ይሰማ ነበረ፤ እግዚአብሔርም ሙሴን ያነጋግረው ነበር (ዘኁል. 7፥89)።

ስለዚህ የጽላቶቹ ማደሪያ የሆነው ታቦት እግዚአብሔር የሚገለጥበት፣ ሕዝበ እስራኤልንም የሚባርክበትየእግዚአብሔር መንበር (ዙፋን) መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ከዚሁም ጋር ይህ ምሥጢራዊ አገላለጽ እንዳለ ሆኖ፣ በግእዙ የክርስቶስ ተከታይም ታቦት ይባላል። «ኢታአምሩኑ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ ወመንፈሰ እግዚአብሔር የኃዳር ላእሌክሙ - እናንተ የእግዚአብሔር ታቦት (መቅደስ) እንደሆናችሁና የእግዚአብሔር መንፈስም እንደሚያድርባችሁ አታውቁምን?» ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቶአል (1ኛ ቆሮ.3-16)። እግዚአብሄርም በሰውም በታቦትም አድሮ ልዩ ልዩ ተአምራትእንደሚሠራ ቀጥለን እንመለከታለን።

## «ታባተ ሕጉ ለእግዚአብሔር» የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት አስደናቂ ተአምር አደረገ።»

### አንደኛው ተአምር

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በእግዚአብሔር ተመርጦና ተሹሞ ሕዝበ እስራኤልን በመሪነት ከአርባ ዓመታት በላይ ካገለገለ በኋላ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ኢያሱን ተክቶ በመቶ ሃያ ዓመቱ ሞተ፤ በቤተ ፌጎር ፊት ለፊት በሞዓብ ምድር በሸለቆ ውስጥ ተቀበረ። የመቃብሩን ትክክለኛ ቦታ ግን ማንም አላወቀውም (ዘዳግ. 34፥ 5-9)።
ኢያሱም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሙሴ እጆቹን ስለ ጫነበት የጥበብን መንፈስ ተሞላ፤ የእስራኤልም ልጆች በሙሉ ታዘዙለት፤ እሱም መሪያቸው ሆኖ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሾመ (ዘዳግ. 34፥10)። እግዚአብሔርም ለኢያሱ እንዲህ አለው፤ «በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ አልጥልህም አልተውህም ...ጽና፣ አይዞህ፣ እጅግም በርታ፣ ባሪያዬ

ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፣ አድርገውም፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደግራም አትበል...» ብሎ አዘዘው (ኢ.ያ.1፥5-9)።

በዚሁ መሠረት ኢያሱ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ሕዝቡ ሰፍሮበት ከነበረው ከሞዓብ ሜዳ ተነስቶ ወደዮርዳኖስ ወንዝ ደረሰ። በዚያን ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ እጅግ ሞልቶ ነበር። ስለዚህም ወንዙን አቋርጦ ወደ ኢያሪኮ መሻገር ፈጽሞ የማይቻል ሆነ፤ በዚሁ ምክንያት ኢያሱ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት፣እጅግ ከመጠን በላይ ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስን ወንዝ አቋርጦ ለመሻገር ሕዝቡን አስለፈ። በመጀመሪያ ግን ታቦተ ሕጉን የተሸከሙ ካህናት ሕዝቡን ቀድመው ወደ ወንዙ እንዲገቡና ውኃውን በእግራቸው እንዲነኩት (እንዲረግጡት) ኢያሱ ለካህናቱ ትእዛዝ ሰጠ፤ በዚሁ መሠረት እንዲህ ሆነ፤ ሕዝቡ ዮርዳኖስን ሊሻገሩ ከየድንኳኖቻቸው በወጡ ጊዜ፣ የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ከሕዝቡ ፊት ሄዱ፤ ዮርዳኖስ ግን እጅግ ሞልቶ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ታቦቱን የተሸከሙ ካህናት በእግሮቻቸው ውታውን ሲነኩ፣ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆሞ፣ እንደ ክምርም ቆሞ ታየ፤ ፈጽሞም ከመፍሰስ ተቋረጠ፤ ሕዝበ እስራኤልም በኢያሪኮ ፊት ለፊት በደረቅ ተሻገሩ። ሕዝቡ በሙሉ እስኪሻገሩ ድረስ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው ነበር (ኢ.ያ. 3፥1-7)።

በእርግጥ ይህ ተአምር እጅግ ድንቅ ነው። የቃል ኪዳኑ ታቦት (ታቦተ ሕጉ) የእግዚአብሔር ስም የተጻፈባቸው ጽላቶች ያሉበት የእግዚአብሔር ማደሪያና የእግዚአብሔር መገለጫ በመሆኑ፣ ከላይ ወደ ታችበከፍተኛ ፍጥነት ግፊት ይጐርፍ የነበረውን የዮርዳኖስን ውኃ ቀጥ አድርጎ አቆመው። ሕዝበ እስራኤልም ያለ ምንም ችግር በደህና ተሻገሩ።

### ሁለተኛው ተአምር

በኢያሪኮ የነበሩት አሕዛብ ሕዝበ እስራኤልን አናሳልፍም ስላሉ፤ ኢያሱ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረትሕዝቡን አሰለፈ፤ ታቦቱን የተሸከሙ ካህናትም ከሕዝቡ ፊት ሆነው መሄድ ጀመሩ፣ ሰባት ካህናትም ከታቦቱ ፊት እየሄዱ ቀንደ መለከት ይነፉ ጀመር። በዚህ ዓይነት ሰልፍ ሕዝቡ ታቦቱን አጅቦ ካህናቱ ቀንደ መለከት እየነፉ ሰባት ቀን የኢያአሪኮን ቅጽር ዞሩ፤ በሰባተኛው ቀን ያ፣ እጅግ ጠንካራ የነበረው የኢያሪኮ ቅጽር ከመቅጽበት ፈረሰ፤ በቅጽሩ ውስጥ የነበሩትም ሰዎች በሙሉ በእስራኤላውያን እጅ ወደቁ፤ ከተማይቱም ተደመሰሰች፤ ፍራሽዋም እስከ ዛሬ ድረስ አለ (ኢ.ያ. 6፥1-21)።

<u>አስተውል</u>፤ እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ አድሮ የዮርዳኖስን ወንዝ ደረቅ አደረገ፤ ሕዝበ እስራኤልም በደረቅ መሬት ተሻገሩ። እንደ ገናም እግዚአብሔር በታቦቱ ላይ አድሮ የኤያሪኮን ግንብ አፈረሰ። ስለዚህ ጽላት ያለበት ታቦት የእግዚአብሔር ዙፋንና የእግዚአብሔር መገለጫ መሆኑን አትዘንጋ።

### ሦስተኛው ተአምር

እስራኤላውያን በካህኑ በኤሊ ዘመን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ገጠሙ። በዘመኑ የነበሩት ካህናት (የኤሊ ልጆች) በኃጢአት ስለረከሱ፣ በዚያ ምክንያት እስራኤላውያን ድል ሆኑ፣ ታቦተ ሕጉም ተማረከ። ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ማርከው ወደ ከተማቸው ወደ አዛጦን ወሰዱት፤ ዳጎንወደ ተባለው ጣዖት ቤትም አገቡት፤ ከዳጎንም ጋር አንድ አድርገው አስቀምጠውት ተመለሱ።በነጋውምየአዛጦን ሰዎች ማልደው ወደ ጣዖቱ ቤት ሄዱ፣ ሲገቡም አምላካቸው ተደፍቶ አገኙት፤ እጅግም አዝነው ዳጎንን ወደ መንበሩ (ወደ ቦታው) መልሰው አስቀምጠውት ሄዱ። ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ (በማግስቱ) በማለዳ ወደ ጣዖቱ ቤት ገቡ። እነሆ ዳጎንን ተሰባብሮና እጆቹና እግሮቹ ተቆራርጠው አገኙት። እጅግም ደነገጡ። በአምላካቸው በዳጎን የደረሰውን አስደንጋጭ ተአምር ተመልክተው «የእግዚአብሔርንታቦት ከከተማችን ውሰዱልን ሕዝባችንን እንዳይጨርስብን ወደ ቦታው መልሱልን» ብለው ጮኹ (1ሳሙ. 5፥1-19)።

<u>አስተውል</u>፣ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት (ታቦተ ሕጉ)፣ የእግዚአብሔር ስም ያለበት፣ እግዚአብሔር የሚገለጥበት (ዘኁል.7፥89) በመሆኑ ሁለት ጊዜ የፍልስጥኤማውያንን ጣዖት ሰባበረ። ስለዚህም የእግዚአብሔር ስም ያለበት ጽላት፣ የእግዚአብሔር መግለጫ የሆነው ታቦት ተአምራት ሠሪ መሆኑን አንርሳ።

### አራተኛው ተአምር

ከፍልስጥኤም ሕዝብ መካከል ቤትሳሚስ የተባሉ ሕዝቦች የእግዚአብሔር ታቦት በዚያ ሳለ በድፍረት ወደ ታቦቱ ቀረቡ፣ በታቦቱ ውስጥ ምን እንዳለ ለማወቅ ወደ ታቦቱ ውስጥ ስለ ተመለከቱ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ቀጣቸው፤ በአንድ ጊዜ ከአምስት ሺህ ሰዎች በላይ ተቀሰፉ (1ሳሙ. 5፥19- 21)።

### አምስተኛው ተአምር

የእግዚአብሔር ሕግ ያለበት ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ በመሆኑ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ተአምራት ከማድረጉም በላይ ዖዛ የተባለው የአሚናዳብ ልጅ እንደ ቤትሳሚስ ሰዎች በድፍረት የእግዚአብሔርን ታቦት እጁን ዘርግቶ ለመያዝ ሞከረ፤ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በዖዛ ላይ ነደደ፤ ወዲያውም እግዚአብሔር ቀሰፈውና ሞተ (2ሳሙ. 6፥3-8)።

### ስድስተኛው ተአምር

የእግዚአብሔር ታቦት ቤትሳሚንና ዖዛን እንደ ቀሰፈ (እንደገደለ) የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ሰምቶና አይቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማው ማስገባትን ፈራ የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ይመጣል? አለ፤ ስለዚህም ታቦቱን ወደ ከተማው ያመጣው ዘንድ አልወደደም። በዚያ ፈንታ ንጉሥ ዳዊት ታቦቱን ወደ ጌት ሰው ወደ አቢዳራ ቤት አገባው። የእግዚአብሔርም ታቦት በጌት ሰው በአቢዳራ ቤትሦስት ወር ያህል ተቀመጠ። እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ።

ንጉሡ ዳዊትም እግዚአብሔር አቢዳራን፣ የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት እንደ ባረከ ሰማ፤ በዚህ ምክንያት ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ከተማው (ወደ ዳዊትከተማ) በታላቅ ደስታ አመጣው (2 ሳሙ. 6፥3-14)።

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው አቢዳራ የእግዚአብሔርን ታቦት በቤቱ በክብር ሰላስቀመጠ እግዚአብሔር አቢዳራን ባረከው፤ ቤቱንም ሁሉ በበረከት ሞላለት፤ ቤተሰቡንም ሁሉ ባረከለት! ይኸውም በእግዚአብሄር ታቦት አማካይነት የተገኘ በረከት ነው። በረከቱም አሰደናቂ ተአምራት ነው።

## ሰባተኛው ተአምር

የእግዚአብሔር ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በታላቅ ክብር በሚወሰድበት ጊዜ ንጉስ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት (በታቦቱ ፊት) የበፍታ ኤፉድ ለብሶ በሙሉ ኃይል ይዘምር ነበር፤ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ሆ! እያሉ ቀንደ መለከትንም እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ አመጡ። የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በገባ ጊዜ የዳዊት ሚስት የሳኦል ልጅ ሜልኮል በቤተ መንግሥቱ መስኮት ሆና ትመለከት ነበር። ንጉሡ ዳዊትንም <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> ሲዘልና ሲዘፍን (ሲዘምር) አየችውና በልብዋ ናቀችው።ከበዓሉም ፍጻሜ በኋላ ንጉሥ ዳዊት ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሰ፤ ባለቤቱ ሜልኮልም ልትቀበለው ወጣችና እንዲህ አለችው፤ «ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገለጡየእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቆነጃጅት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው» በማለት ነቀፈችው።ዳዊት ግን ለሜልኮልን እንዲህ ሲል መለሰላት፤ «በእግዚአብሔር ፊት ዘፍኛለሁ (ዘምሬያለሁ) ፣በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር ይመስገን፣ ስለዚህም ከሆንሁት ይልቅ የተናቅሁ እሆናለሁ (የተናቅሁ ልሁን)፣ በዓይንሽም የተዋረድሁ እሆናለሁ፣ ነገር ግን እንደ ተናገርሽው በቆነጃጅቱ ፊት ግን እከብራለሁ» አላት። ከዚህም የተነሳ የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም (2ሳሙ. 6፥12-23)።

<u>እናስተውል</u>፤ ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው ንጉሥ ዳዊት ያመስገነውና፣ እየዘለለም የዘመረው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ነበር፤ ታቦቱም የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑን ለማስገንዘብ «በእግዚአብሔር ፊት ዘምሬያለሁ» በማለት ለሜልኮል መለሰላት። በዚህ ታሪክ ለታቦት ምስጋናና ዝማሬ ማቅረብ ለእግዚአብሔር ማቅረብ መሆኑን እንገነዘባለን።

ነገር ግን ለሳኦል ልጅ ሜልኮል እግዚአብሔርን ከማክበር ይልቅ ራስዋን ማክበርና ከፍ ከፍ ማድረግ የበለጠ መሆኑን ስለ መረጠች፤ ከእግዚአብሔር በረከት ወጣች፣ የእግዚአብሔር ስጦታ (ጸጋ) የሆነውንም ልጅ (መዝ. 126 (127)፥3) ሳታገኝ ቀረች መካን ሆናም ሞተች። ይኸውም ታቦትን ከመናቅ የመጣ ቅጣት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

### «የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አይሻርም»

በብዙ ስምና በብዙ አጠራር የሚጠራው እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ሕያውና ዘላለማዊ አምላክ ነው። «እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው፣ እኛም አናውቀውም (አንደርስበትም)፤ የዘመኑ ቁጥርም አይመረመርም» በማለት ጻድቁ ኢዮብ አስረድቶአል (ኢዮብ 36፥26)። ንጉሥ ዳዊትም እግዚአብሔር ዘለዓለም የሚኖር የማያልፍና የማይለወጥ መሆኑን ሲመሰክር፤ «አንተ ግን (አንተ እግዚአብሔር ግን) ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» ብሎአል (መዝ. 101 (102) ፥27)።

በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦትም የእግዚአብሔር ሕግ ያለበት የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለ ሆነ፣ አይሻርም። ጽላት የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት በመሆኑ ክብሩም ሆነ ቅድስናው አይሻርም።

በዘመነ ብሉይ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በካህናቱ አማካይነት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ ሲሄድ ወይም ከአንድ ሰፈር ው ሌላው ሰፈር ሲገባ ሕዝቡ እግዚአብሔር ገባ እያሉ ይደነግጡና እግዚአብሔርን ይፈሩ ነበር።

ባንድ ወቅት እስራኤላውያንና ፍልስጥኤማውያን ጦርነት ገጠሙ፤ ካህናቱ አፍኒንና ፊንሐስም የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ጦር ግንባሩ ወሰዱት፤ ታቦቱ ወደ እስራኤል ሰፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ፤ ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ እስራኤላውያን ሰፈር መግባቱን አስተዋሉ፤ ፈርተውም«እግዚአብሔር ወደ ሰፈር መጥቶአል» አሉ(1ሳሙ. 4፥5-8)።

ነቢዩ ሙሴም እስራኤላውያንን በምድረ በዳ በሚመራበት ወቅት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት (ታቦተ ሕግ) በተጓዘ ጊዜ «አቤቱ፣ ጌታ ሆይ፣ ተነሣ፣ ጠላቶችህም ይበተኑ፣ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ» እያለ ይዘምር ነበር፤ ታቦተ ሕጉም ባረፈ ጊዜ «ጌታ ሆይ፣ ወደ እስራኤል እልፍ አእላፋት ተመለስ» እያለ ይዘምር ነበር (ዘኁል. 10፥35)።

ስለዚህ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያና መገለጫ በመሆኑ ሥርዓተ ታቦት የሚያልፍና የሚሻር አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጽላተ ሕጉ የተጻፈው ሕገ ኦሪት፣ በነቢያት አንደበት የተነገረው ትንቢትና ትምህርት የማይሻርና የማያልፍ መሆኑን አስተምሮናል፣ እንዲህ ሲል - «እኔ ሕግንና (ኦሪትን) ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምስላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም» በማለት አሰተምሮአል (ማቴ. 5፥17- 19)።

ከኦሪት ሕጎች መካከል የመጀመሪያውን ቦታ የያዙ አሥሩ ሕግጋት (አሥሩ ቃላት) ወይም አሥሩ ትእዛዛት ናቸው። እነዚህም ትእዛዛት (ሕግጋት) ሙሴ በደብረ ሲና ከእግዚአብሔር እጅ ከተቀበላቸው ትእዛዛት መካከል ዋናዎቹ መሆናቸው የታወቀ ነው። እነዚህ ትእዛዛት መሪ ትእዛዛት (መሪ ሕጎች) በመሆናቸው፤ እግዚአብሔር በጽላቶቹ ላይ ጽፎ ለሙሴ እንደ ሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዘጸአ. 34፥28)። ስለዚህ የዘመኑ ተከራካሪዎች በአሁኑ ጊዜ ዘመኑ የወንጌል ጊዜ፣ የሐዲስ (ዘመነ ሐዲስ) ስለሆነ የሥርዓተ ታቦት ወይም የክብረ ታቦት መኖር አስፈላጊ አይደለም ይላ

ሉ፤ በዚህም አባባላቸው በዚህ ዘመን የሕግጋት (የሕጎች) ሁሉ መሠረት የሆኑት አሠርቱ ቃላት (አሥሩ ሕግጋት) አያስፈልጉም ማለታቸው ነው።

ጌታችን ግን ስለዚሁ ሲያስትምር «እኔ ሕግንና (ኦሪትን) ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም (ልፈጽማቸው) እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ (ከኦሪት) አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፣ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከእነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን እንኳን የምሽር፣ ለሰውም እንዲህ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፣ የሚያደርገውና የሚያስትምረውም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል» በማለት አስረድቶናል (ማቴ. 5፥17-20)።

በዚሁ መሠረት «ኦሪት አልፋለችና ታቦተ ሕጉ መከበር የለበትም፣ ጽላተ ሕግ አያስፈልግም፣ አሥርቱ ቃላት አያስፈልጉም» እያለ የሚያስተምር ካለ ጌታችን እንዳለው፤ ያ ሰው በመንግሥተ ሰማያት ዕጣ ክፍል የለውም።

አቡነ ገብርኤል «ክብረ ቅዱሳን» በሚል ርዕስ በ1990 ካሳተሙት የተወሰደ።